ከኢትዮጵያ የምግብና መድኃኒት ባለሥልጣን
ጋር በመተባበር በየ15 ቀኑ የሚታተም

# ‹‹ከተሞችን ከትምባሆ ጭስ ነፃ የማድረግ ሥራ ቀጣይነት ያለው ክትትልና ቁጥጥርን ይጠይቃል››

### የኢትዮጵያ ምግብና መድኃኒት ባለሥልጣን ዋና ዳይሬክተር ሄራን ገርባ

ትምባሆ አጫሽነት ወይም ተጠቃሚነት በዓለም ላይ በየዓመቱ ከ8 ሚሊዮን በላይ ሰዎችን ለሞት ከሚዳርጉ ትልልቅ የሕዝብ ጤና ችግሮች ውስጥ አንዱ ነው። መረጃዎች እንደሚያመላክቱት በትምባሆ ጭስ ተጠቃሚነት ምክንያት ከሚሞቱት ሰዎች ውስጥ ከ7 ሚሊዮን በላይ የሚሆኑት በቀጥታ ትምባሆን የሚያጨሱ ሲሆኑ ከ1 ሚሊዮን በላይ የሚሆኑት ደግሞ ለጭሱ በተለያየ መንገድ የሚጋለጡ ናቸው።

በማንኛውም መንገድ ትምባሆን ማጨስ እና በየትኛውም ደረጃ ለትምባሆ ጭስ መጋለጥም ሆነ ማጨስ አደጋው አስከፊ ነው። በኢትዮጵያም ይህን ታሳቢ በማድረግ ከተሞችን ከትምባሆ ጭስ ለመከላከል የተለያዩ ተግባራት በመከናወን ላይ ናቸው።

በባለፈው እትማችን አዲስ አበባ ከተማን ከትምባሆ ጭስ ነፃ ለማድረግ እየተከናወኑ ያሉ ሥራዎችን በተመለከተ ከኢትዮጵያ ምግብና መድኃኒት ባለስልጣን ዋና ዳይሬክተር ከወይዘሪት ሄራን ገርባ ጋር የተደረገ ቃለ-መጠይቅ ይዘን መቅረባችን ይታወሳል።

በዛሬው እትማችንም በተለይም ኢንሼቲቩ በተጨባጭ ያመጣው ውጤት ምንድን ነው? ትክክለኛ መረጃ በማስተላለፍ ረገድ ምን ጥረት እየተደረገ ነው? በሚል ላነሳነው ጥያቄ ዋና ዳይሬክተራ የሰጡን ምላሽ እንደሚከተለው ይዘን ቀርበናል።

ዋና ዳይሬክተራ እንደሚገልጹት፣ ይሄ ኢንሼቲቭ የሚያመጣው ውጤት በብዙ መልኩ ሊቃኝ የሚችል ነው። ከፍተኛ የገንዘብን ወጪን መቀነስ ብሎም ማስቀረትም አንደኛው ነው። እንደሚታወቀው፣ የትምባሆ ማጨስ ተላላፊና ተላላፊ ያልሆኑ በሽታዎች ምክንያት ነው። ካንሰርን ጨምሮ አጠቃላይ ከመተንፈሻ አካላት ጋር የተያያዙ ችግሮችን ያስከትላል። የትምባሆ ጉዳቱ የሚያጨሱት ብቻ ላይ አይቆምም። በቀጥታ ማያጨሱ ሰዎች/Second hand



smokers/ችንም ለተለያዩ የጤና ችግር ያጋልጣል።

በዓለም በየዓመቱ በትምባሆ ምክንያት ከሚሞቱ አንድ ሦስተኛው ከሁለተኛ አጫሽነት ጋር የሚገናኝ ነው። እነዚህ ተላላፊ ያልሆኑ በሽታዎች ከፍተኛ ገንዘብ የሚያስወጡ ናቸው። ለምሳሌ ካንሰር የረጅም ጊዜ ሕክምና ይጠይቃል። የመተንፈሻ አካላት ችግርም የዘላለም በሽታ ነው።

ሌሎችም ከትምባሆ ጭስ ጋር የሚገናኙ በሽታዎች በሙሉ አንዴ መድኃኒት ተወስዶ የሚድኑ አይደሉም። ይሄ ከታማሚው ባሻገር በመንግሥት ላይ የሚያስከትለው የጤና ወጪ በጣም ከፍተኛ ነው። አሁን ባለው የአገራችን ሁኔታ የተላላፊ በሽታዎች ስርጭት በአብዛኛው ከሃምሳ በመቶ በላይ እየሆነ ያለው። የኅብረተሰቡ የጤና ፍላጎት በጣም እያደገ ነው። እነዚህ ሁሉ ሲደመሩ በጣም ከፍተኛ ጫና ይፈጥራል።

የትምባሆን ስርጭት የመቀነስ ጉዳይ ከእዚህ ጋር የሚገናኝ ነው። ምናልባት በእነዚህ ሁሉ ሥራ ምን ያህል የአጫሽ ቁጥር ቀንሷል የሚለውን መመልከት ያስፈልጋል። እ.ኤ.አ በ2016 የመጨረሻው የግሎባል አደልት ቶባኮ ሰርቬይ 15 ዓመትና ከዚያ በላይ ያሉ የማኅበረሰብ ክፍል የማጨስ መጠኑ ምን ይመስላል የሚለው 5 በመቶ ይጠጋል። 5 በመቶ ማለት ከኢትዮጵያ ሕዝብ አንፃር ከፍተኛ ቁጥር ነው። በዚህ ረገድ አሁን ጥናት ጀምረናል። ካለማጨስ ምን ያህል ተጠብቀዋል፣ ምን ያህል ወጪ ቀንሷል የሚለውን ጥናት ውጤትም በቀጣይ የምናየው ይሆናል። አሁን ላይ ግን ቢያንስ የጤና ጉዳቱን ይቀንሳል ብለን እናስባለን።

ሁለተኛ ሪፖርት ከማድረግ አንፃር ይሄን ሥራ ስንሰራ እራሳችን አመራሮቹ አዲስ አበባን እየዞርን እናያለን። ባርና ሬስቶራንቶች፣ በተለይ የምሽት ክለቦች ተቆጣጣሪው የሚሠራው ቀን ነው። ቀን ላያስጨሱ ይችላሉ። ነገር ግን ማታ በድብቅ ሊፈፀም ይችላል።

ምናልባት በዚህ አጋጣሚ የራሴን ልምድ ለመናገር አንድ ክልል ላይ ከትምባሆ ጭስ ነፃ የሆነ ቦታ አሳዩኝ ብዬ ስጠይቅ እንዳይጨስ የተሻለ ያስተገበረ ነው ብለው አንድ ሬስቶራንት ወሰዱኝ። በኋላ ግን እኔ ለመፈተን «እዚህ ሬስቶራንት ማጨስ እፈልጋለሁ ይቻላል ወይ» ብዬ ጠየኩኝ ።

«ክልክል ነው፣ ግን እናመቻችሎታለን ብሎ ደበቅ ያለ ቦታ ላይ ወንበር አዘጋጁልኝ።» ይህ እንግዲህ ከይሉኝታም ሊሆን ይችላል። ይሁንና እዚህ ላይ የተረዳሁት ነገር ቢኖር ምን ያህል ሪፖርቱን ማረጋገጥ እንደሚያስፈልግ ነው። ዝም ብሎ አታስጨሱም ታስጨሳላችሁ ማለት ብቻ ሳይሆን ቦታው ተገኝቶ መፈተሽ ያስፈልጋል።

የዚህ ኢንሼቲቭ ከየክልሉ እንደሚመጣልን ሪፖርት ሙሉ በሙሉ ነፃ ነው የሚባለው ከፍተኛ ነው። ይሁንና በአንድ ጊዜ በእይታ ብቻ ነፃ ነው ማለት አይደለም። በጣም በድግግሞሽና ቀጣይነት ባለው ሁኔታ ቁጥጥር በማድረግ ወደ ሥርዓት ማስገባት ያስፈልጋል።

አንዳንድ ቦታዎች ስንመለከት እንደዚህ ዓይነት ችግሮች ሊያጋጥሙ ይችላሉ። ትልቁ ነገር በእኛም ደረጃ በአዲስ አበባ ምግብ፣ መድኃኒት፣ ጤናና ጤና ነክ ግብዓቶች ቁጥጥር ባለሥልጣን በአመራሮች ደረጃ ወደታች እየተወረደ የማረጋገጥ ሥራ ይሠራል። የሌሊት የቁጥጥር ሥራም ይሠራሉ።

ይሄ የሌባ እና ፖሊስ ጨዋታ አይደለም። የግል ዘርፍ ባለቤት መሆን አለበት። ኅብረተሰቡ በበለጠ ሕግ ስለወጣለት ትምባሆ እንዳይጨስብኝ ብሎ መጠየቅ አለበት። ሁሉም ይሄን ጉዳይ በባለቤትነት ካልያዘ በተቆጣጣሪው አካል ብቻ ሊፈጸም አይችልም።

ለአብነት በዚህ ዓመት ከየክልሉ የደረሰን ጥቅል ሪፖርት ከትምባሆ ጭስ ነፃ መሆን ያለባቸው ከ 64 ሺ በላይ ተቋማት ኢንስፔክት ተደርገዋል የሚል ነው። ይህ ትልቅ ቁጥር ነው። ይህን ማረጋገጥ ያስፈልጋል። የዚህን ቀጣይነት ያለው የክትትልና ግምገማ ሥርዓታችንን አጠናክረን መሄድ አለብን። ይሄ ኢንሼቲቭ ውጤታማ ነው የሚባለው ከነበርንበት ሲታይ ካልሆነ በስተቀር አሁንም ክትትል ካልተደረገበት የሚመጣው ሪፖርትና መሬት ላይ ያለው ሊለያይ ይችላል።

ከኢትዮጵያ ምግብና መድኃኒት ባለሥልጣን ዋና ዳይሬክተር ሄራን ገርባ ጋር የተደረገ ቃለ-መጠይቅ ቀጣይ ክፍል በሚቀጥለው እትማችንም ይዘን የምንቀርብ መሆኑን እናስታውቃለን።

Tel : +251-11-552-41-22
+251-11-552-41-22
P.o.box. 5681
Free call. 8482
http://www.fmhaca.gov.et/contact/
E-mail contactefda@efda.gov.et
Telegram channel link
https://t.me/ethiopianfoodanddrugauthority/

በብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት ታተመ